# የባድመ ምስጢር

(ወንድወሰን ተክሉ-ኢትዮሚዲያ አምደኛ)

## **የኢትዮጵያና ኤርትራን ግንኙነት ማሻሻል ይቻላል?

(ክፍል አንድ)

"በእኛ በኢትዮጵያዊያን ላይ በባድመ ስም የተፈጸመብን ጥፋትና ክህደት ትውልድ ሁሉ የመለስን ስም እንዲረግም ያደርገዋል»

የዛሬ መጣጥፌ የሚያነጣጥረው በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ያለውን የNo peace, No war ፖሊሲን ለመለወጥና ብሎም የሁለቱን ህዝቦች ግንኙነት ወደ ጤናማ ጉርብትና ደረጃ Normalization ለማድረስ የተለያዩ ኋይሎች እያሰቡና ብሎም እየተንቀሳቀሱ ባሉበት በዚህን ወቅት በግንኙነቱ ላይ የበርሊን ግንብ ያህል ጎልቶና ጠንክሮ በሁለቱ ህዝቦች መካከል ተገንቦቶ ያለውና ሊያቀራርብም ያልቻለውን የባድመ ጉዳይ የተመለከተ መጣጥፍ እንደሆነ ከወዲሁ ላሳውቅ እወዳለሁ፡፡

የኢትዮጵያንና የኤርትራን ግንኙነት በመወሰን ደረጃ ታላቅ ድምጽና ኋይል ያለው ኡየባድመ ጉዳይ በመሆኑ ይህንን «የባድመ ምስጢር» በሚል አርእስት ስር የመጀመሪያና ክፍል አንድ የሆነውን የዛሬ መጣጥፍ ላቀርብላችሁ ወድጄ እነሆኝ ብያለሁ፡፡

***መነሻ ጭብጥ-የባድመ አስኳልነት

ባድመን ውድ ልጆቻችንን መስዋእት ባደረግንበት ጦርነት አስመልሰን እና ተቆጣጥረን ሳለ በምስጢራዊው የአልጀርስ ስምምነት ፈራሚው መለስ ዜናዊ ምክንያት ተመልሰን የተነጠቅን የደም መሬታችን መሆኗን ሁላችንም የምንረዳ ይመስለኛል፡፡

እንዴት ነው ባድመ ተጥቅላላ ሄዳለች እንዴ «ያጣናት» የምትለው ብላችሁ ጥያቄ የምታነሱ ትኖራላችሁ፡፡ መልሱ እነ ወዲ ዜናዊ ተስማምቶ፣ፈቅዶና ወዶ በፈረመው «ህግ» መሰረት የኤርትራ ስትሆን ንብረትነቷ ግን በጉልበትም ቢሆንና ለጊዜውም በእኛ ግዛት ስር ያለች የደም መሬት እንደሆነች እንረዳለን፡፡

የባድመ ጉዳይ በሁለቱም ወገኖች በኩል እጅግ ወሳኝ ከመሆኑ የተነሳ ያኔ ከሃያ ዓመት በፊት ከፍተኛ እልቂት ላስከተለው ጦርነት መነሻ መንስኤና ምንጭ የመሆና ያህል ዛሬም ሆነ ነገ ለጦርነቱ ፍጻሜና ብሎም ለመታረቅና ላለመታረቅ በብቸኝነት ደረጃ መወሰን የሚቻለው ይህው የባድመ ጉዳይ ከመሆኑ የተነሳ ባድመን የሁሉ ነገሮች-ማለትም፤የሰላምና ጦርነት፣የእርቅና አለመታረቅ፣የሽንፈትና ማሸነፍን ሚናን በመተወን የኋይልን ሚዛን የምትለካም የሁሉ ነገር አስኳል ነች-ባድመ፡፡

ሁሉቱም ወገኖች ይህ ቀረሽ የማይባል ዋጋ የከፈሉባት፤በሁለቱም ስርዓቶች ውስጥ መፈንቅለ መንግስት መሰል ክፍፍል የተፈጠረባት የባድመ ጉዳይ ለሁለቱም ገዢ ኋይሎች የስልጣን እና

የህልውናንም ሁኔታን በመወሰን ደረጃ ወሳኝ ኋይል በመሆን ከአንበሳው ድርሻ ውስጥ የአስኳሉን ሚናን የምትጫወት ኋይል እንዳላት እንረዳለን፡፡

የባድመ ጥያቄ ሳይመለስ የሁለቱ ሀገራትን ግንኙነት ማስተካከል ይቻላልን?
--

ለስድስት ዓመታት የዘለቀው የሁለቱ ድርጅቶች ማለትም የህወሃትና ሻእቢያ የጫጉላ ሽርሽር ያከተመበት ሁኔታና ስፍራን ብዙዎች ባድመ ናት ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ ከእፍ ካስባለው የሁለቱ እከክልኝ ልከክልህ ፍቅር መጨንገፍ በኋላ በሁለቱም ወገን በኩል ላለቀው ከ70ሺህ በላይ ውድ ነፍሳት ምክንያት ተጠቃሿ ባድመ ከመሆኗም ባሻገር ላለፉት ሁለት ዓስርተ ዓመታት ያህል በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ያለውን ግንኙነት ወደ Normalization ለመለወጥም የበርሊን ግንብ ያህል በመካከላቸው ተገንብቶ ያለው የባድመ ምስጢር እንደሆነ የአደባባይ ገበና ነው፡፡

ህወሃት 17ዓመት በፈጀው ትግል ወደ 60ሺህ የሚጠጉ ታጋዮችን መስዋእት አድርጌያለሁ በማለት የትኛውንም መጥፎም ይሁን መልካም ስራን በተሰውት ስም እየማለ ሲፈጽም እናያለን፡፡ በ17ዓመቱ አስከፊ ትጥቅ ትግል 60ሺ መስዋእት በማድረጉ የተቆረቆረና እጅግ ያዘነ የሚመስለው የህወሃት አመራርና ካድሬ ወራቶችን ብቻ ባስቆጠረው የባድመ ጦርነት ላይ ግን ከ70ሺህ በላይ ሀገር ወዳድ ቅን ዜጎች ለተሰውበት ይህን ያህልም ያዘነ፣የተቆረቆረና የተጸጸተ ያልመሆኑ እውነት አስደንጋጭ ቢሆንም ድርጊቱ ግን እውነት የሆነ ያለ ሀቅ ነው፡፡

የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች የሆኑትና የነበሩት ህወሃትና ሻእቢያ ለእርቅ እንኳን በማይመችና አዳጋች በሆነ ደረጃ ያንን ሁሉ እልቂትን ያስተናገደን ጦርነት እንዴት ሊፈጥሩ ቻሉ? ብለን ስንጠይቅ በእርግጥ ውሃ እሚቋጥሩ በርካታ ኩነቶችና ሂደቶች ቢኖሩም የክስተቶቹ ክምችት ማራገፊያ ግን ባድመ እንደሆነች ሁሉም የሚስማማበት ሁኔታ ነው፡፡

እራሱን የህወሃት ሊቀመንበር አድርጎና በፈጠረው ኢህአዴግ ስም እራሱን የኢትዮጵያ ጠ/ምኒስትር ያደረገውና «አንድ መጽሀፍ ከማንበብ ሃያ ደቂቃ ከአቶ ኢሳይያስ ጋር ማውራት ይበልጥ ያስተምራል» ያለው መለስ፡ ከኢትዮጵያዊነቱ ይልቅ ኤርትራዊነትን የመረጠው መለስ የሀገሪቱ ጠ/ም ሆኖ ሳለ እንዴት የሁለቱ ኋይሎች ፍቅር ወደ ለእርቅ የሚያስቸግር ጦርነት ውስጥ ሊገባ ቻለ የሚለው ወሳኝ ጥያቄ መልስ ለብዙዎች ዛሬም ድረስ እንቆቅልሽ የሆነ ያህል እማይታወቅና የተድበሰበሰ ነው፡፡

በግንቦት ወር 1990ዓ.ም ላይ ባድመ በሻእቢያ ሰራዊት ቁጥጥር ስር ዋለች፡፡ በወቅቱ ሀገሪቷ ድንበር ጠባቂ የመከላከያ ሰራዊት አልነበራትምና በሜካናይዝድ የተደገፈው የሻእቢያ ሰራዊት ወረራ ከኢትዮጵያ በኩል ብዙም ተቃውሞ ሳይገጥመው ባድመን ለመቆጣጠር እንደበቃ ይታወቃል፡፡

ኤርትራዊው አቶ መለስ (ለምንድነው የኢትዮጵያ ግዛት በሆነችው ትግራይ አድዋ በአባቱ ኢትዮጵያዊ በእናቱ ኤርትራዊ ሆኖ የተወለደውንና ኢትዮጵያን ለ21ዓመታት የገዛትን ለገሰ ዜናዊ አስረስ ኤርትራዊ እያልኩ ልገልጸው የቻልኩት? እኔ አይደለሁም ይህ የለገሰ ዜናዊ ምርጫና ውሳኔ ስለሆነ እንጂ የእኔ አገላለጽ አለመሆኑን እየገለጽኩ ይህም እንዴት ሊሆን እንደቻለ በሂደት እንደማሰፍረው ልገልጽ እወዳለሁ) ሀገሪቷን ድንበር ጠባቂ አልባ ያደረጋት በመጀመሪያ በ1983ዓ.ም አዲስ አበባን ሲቆጣጠር የኢትዮጵያን መከላከያ ሰራዊት ማለትም የምድር ጦር፣የባህር ኋይልና የአየር ኋይሉን ክፍል ሙሉ በሙሉ በማፍረስ በጎዳና የበተነው ሲሆን ህወሃትን/ኢህአዴግን ለስልጣን ያበቃውን የራሱን ሰራዊት ደግሞ ቆየት ብሎ ከ1985ዓ.ም ጀምሮ -

1ኛ-የገበሬ ሚሊሺያ ስለሆነ ወደ ሀገር መከላከያ ሰራዊትነት ደረጃ መታቀፍ አይቻልም በማለት-

2ኛ-ሀገራዊ ህብረ ብሄር መከላከያ ሰራዊት ለመገንባት አብዛኛው የህወሃት ታጋይ መቀነስ አለበት በሚል ሰበብ እስከ 1990ዓ.ም ድረስ አቶ መለስ በትንሹ ከ80ሺ.ህ ያላነሰ ይህወሃት/ኢ.ህአዴግን ሰራዊት በማፍረስ ከ50ሺ.ህ ባነሰ ሰራዊት የሀገር ድንበር በሚጠበቅበት ወቅት ነው ሻእቢያ የባድመን ወረራ ፈጽሞ ሊቆጣጠር የቻለው፡፡

ከግንቦቱ 1990ዓ.ም የሻእቢያ ወረራ በፊት ለወረራው ግብዓት የሆኑና ያገለገሉ በርካታ ኩነቶችና ክስተቶች በሁለቱ ድርጅቶች መካከል የተፈጠረ ሲሆን ይህም ድህረ ባድመ ጦርነት የነበረው የሻእቢያ ኢኪኖሚያዊ ጥቅምና ፖለቲካዊ የበላይነት እየወደቀ መምጣጥት ለወረራው መፈጸም ትልቁን ሚና እንደተጫወተ ብዙዎች ደጋግመው ሲገልጹት የሰማን ሲሆን ለሻእቢያ ግን ለወታደራዊ እርምጃው ቁልፍ ጥያቄን የባድመን የባለቤትነት ጥያቄን በማንሳት እንደሆነ አይተናል፡፡

ወረራው ያስቆጣቸው ሀገር ወዳድና ሀገር አፍቃሪ ኢትዮጵያዊያንም በአቶ መለስ ክህደትና ጸረ ኢትዮጵያዊ አቋምና ስራው የቱንም ያህል አንጀታቸው የበገነ፣ጨጓራቸው የተላጠና ንዴታቸውም የተንተገተገ ቢሆንም የ«ሀገር ጉዳይ የህልውና ጉዳይ ነው» በማለትና ይህንን ቁስላቸውን ችለው ሀገራቸውን ለመታደግ እጅግ ተረባረቡ፡፡

ሻእቢያ ድንበራችንን ደፈረ በማለትና ብሎም «ከባድመ መልስ ወደ መለስ» በሚል መሪ መፈክር ኢትዮጵያዊያኑ የሀገራቸውን ዳር ድንበር ለማስከበር ልክ አያት ቅድመ አያቶቻቸው እንዳደረጉት እነሱም በወኔና በሞራል ከዳር እስከ ዳር በመነቃነቅ ወደ ባድመ ዘመቱ፡፡

ይህ የባድመ ጦርነት ከመከሰቱ ስድስት ዓመት ቀደም ብሎ ልክ እንዳረጀና እንደተበሳሳ ጥቅም አልባ ቁና ተብሎ የተሽቀነጠረው የቀድሞ መከላከያ ሰራዊት እንኳን ሳይቀር በታላቅ ወኔና ጀብድ በዘመቻ ባድመ ላይ ሲሳተፉ ባየንበት ወታደራዊ ዘመቻ ኢትዮጵያ ከየካቲት 1991ዓ.ም ጀምሮ በ«ዘመቻ ጸሀይ ግባት» ኦፕሬሽን ባድመን ጨምሮ ዛላአንበስንና አጠቃላይ የተያዙባትን ግዛቶች መልሳ መቆጣጠር የቻለች ቢሆንም የተከፈለው መስዋእትነትና የታየው እልቂት ግን እጅግ ከፍተኛና አሰቃቂ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

ጦርነቱ በምስራቅ ግንባር በአሰብ ቡሬ፣ በምእራብ በመተማ ግንባር እና በዛላአንበሳ፣ሽሬ፣በጸረናም ጭምር የተካሄደ ካባድ ውጊያ ቢሆንም ባድመን ብቻ ለማስለቀቅ በተካሄደው ዘመቻ እስከ 30ሺ.ህ ንጽሃን ዜጎቻችንን እንደገበርን ወታደራዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ጦርነቱ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ እንደሚካሄድ ዘመናዊ ውጊያ የታየበት ሳይሆን ልክ ከ1ኛው የዓለም ጦርነት በፊት እንደነበሩት በርካታ አሰቃቂ ኋላቀር ውጊያዎች በተጠመደ የፈንጂ ወረዳ ላይ የሰው ልጅ ተረማምዶ እንዲያልቅ የተደረገበትና እጅግ ከፍተኛ የሆነ ኋይለኛ እልህ፣ንዴት፣ ቁጭትና አልደፈር ባይነት ስሜቶች የተቀጣጠለን ወራሪን ኋይል በእጅ ለመተናነቅ የወገን ሰራዊት በጸረ ሰው ፈንጂ እጅግ የተጠናከረውን የሻእቢያን ምሽግ ልጆቻችን ተረማምደው መስዋእት በመሆን ምሽጉን ሊሰብሩ እንደቻሉ ተናግረዋል፡፡ ይህችን የሬክታንግል ቅርጽ ያላትን መሬት ለማስለቀቅ የተከፈለው መስዋእትነት እጅግ ልብ የሚነካ ከባድ ክፍያ እንደሆነ የዓይን ምስክሮችና መረጃዎች ይገልጻሉ፡፡

የተሰበረውን የባድመ ምሽግ ሻእቢያ ከጦርነቱ በፊት ከሶሪያ፣ኢራቅና ግብጽ በጋበዛቸው ወታደራዊ ጄኔራሎችና ጠበብቶች የባድመን ምሽግ ከጎበኙ በኋላ በሰጡት አስተያየት ይህን ምሽግ ስብሮ የሚገባ ኋይል አይኖርም ያሉ ሲሆን ሻእቢያም ይህን ማረጋገጫ ተከትሎ «ባድመ የኢትዮጵያ ሆነች ማለት ጸሀይ አገልግሎቷን አቁም በቀን ጠለቀች ማለት ነው» ሲል ገልጾ ነበር፡፡

ይህን መሰረት ያደረገው የኢትዮጵያ ባድመን የማስመለስ ወታደራዊ ፕላን «በዘመቻ ጸሀይ ግባት» ስም ለመሰየም የተቻለ ሲሆን  ከባድመ ጀምሮ በመተማ በኩል በኡምሃጀር አድርጎ እስከባሬንቱ ድረስ ስንቆጣጠር ወይም በዛለአንበሳ በኩል እስከ ሰንአፌ ድረስ ስንቆጣጠርና በተሰነይ በኩል በሱዳን ወደ አስመራ ለመቃረብ በተደረጉት ውጊያዎች ከከፈልነው መስዋእትነት  ይልቅ አንዲት «መንደር» እየተባለች የምትጠቀሰዋን ባድመን ለማስለቀቅ በተደረገው ውጊያ የከፈልነው የሰውና የንብረት መስዋእትነት እጅግ የጎላና ከፍተኛ ዋጋ እንደሆነ ነው መረዳት የሚቻለው፡፡

**በ30ሺህ ውድ  ኢትዮጵያዊያን ውድ ህይወት፣ደምና አጥንት ነጻ የወጣችው የባድመ እጣፈንታ ምን ሊሆን ይችላል? ይህች ትራያንግላማዋ መንደር የማንናት?

የ41ዓመቱ አንደበተ ርቱእ ዶ/ር አቢይ አህመድ ወደ ስልጣን ከመጡ ገና 40ቀን እንኳን ያልሞላቸው ቢሆንም በዚሁ አጭር ቆይታቸው በጅቡቲ፣በኬኒያና በሱዳን ይፋዊ ጉብኝት ያደረጉ ሲሆን በሚደንቅ ሁኔታና ተመሳሳይነት ባለው መልኩ ከሶስቱም ሀገራት መሪዎች ጋር ከወደብ ጋር በተያያዘ ስምምነት የማድረጋቸው ጉዳይ ሲሆን ድርጊቱም የወደብ ጉዳይ ክፉኛ ሰንቆ እንዳሳሰባቸው አመላካች እንደሆነ ነው እሚያስረዳው፡፡

ከመቶ ሚሊዮን ህዝብ በላይ የሚኖርባት ወደብ አልባዋ ሀገራችን ኢትዮጵያ ጠ/ም ሆኖ ለተቀመጠ ሰው የወደብ ጉዳይ ባያስጨንቀው (አሊያም እነደ መለስ ከሀዲ ካልሆነ በስተቀር ማለቴ ነው)ብቻ ነው እሚያስደንቀው እንጂ የዶ/ር አቢይ በወደብ ጉዳይ ተጨንቆ ከኬኒያ፣ጅቡቲና ሱዳን ጋር በወደብ ነክ ጉዳዮች ላይ ስምምነትን መፈረምና ብሎም በቀጣይ ከሶማሌ ጋርም በተመሳሳይ ሁኔታ ስለወደብ ለመፈራረም መዘጋጀት የሚጠበቅ ሲሆን ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ያለውን ግንኙነት አሁን ካለበት የNo peace, No war ፖሊሲ ወደ Normalization ደረጃ ለማሳደግ ፈቃደኝነታቸውን ማሳየታቸው ምን እቅድና ፕላን አዘጋጅተው ነው ከኤርትራ ጋር ለመታረቅ ደጅ እሚጠኑት እንድንል አድርጎናል፡፡

ለጅቡቲ ወደብ በዓመት ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ የምታስገባው ወደብ አልባዋ ኢትዮጵያ እንድሜ ለመለስ ዜናዊ «ወደብ አያስፈልገንም » ብሎ የአሰብን ኢትዮጵያዊነትን አሽቀንጥሮ  ኤርትራዊነትን ላስለበሰ ይሁንና ኢትዮጵያ ዛሬ በወደብ ነክ ጉዳዮች ላይ ብትቅበዘበዝና ብሎም በየሄደችበት ከጎረቤቶቻ ጋር ለመደራደር ስትቃትት ማየት ቢያሳዝነኝ እንጂ አያስደንቀኝም፡፡

(በነገራችን ላይ በ1991 የሎንደኑ ኮንፍረስ በአይሁዳዊው ሄርማን ኮህን አደራዳሪነት ሻእቢያ፣ ህወሃትና ኦነግ በወደፊቷ ኢትዮጵያ ህልውና እጣፈንታ ላይ ሲወስኑ አይሁዳዊው ሄርማን ኮህን አሰብን በኢትዮጵያ ውስጥ እንድትካተት ያቀረበውን ሀሳብ አምርሮ የተቃወመውና ያስከለከለው ኢሳይያስ ሳይሆን መለስ ዜናዊ እንደሆነ አይሁዳዊው በመጽሃፉ ተናዟል፡፡ መለስ በስልጣን ላይ በነበረበት ዘመኑ ከሁሉ በላይ እጅግ እሚያንገሸግሸውና እንደ ህመምተኛም እሚያንቀጠቅጠው የአሰብ ጉዳይ ሲነሳ እንደሆነም እናስታውሳለን)

አዲሱ ጠ/ም ዶ/ር አቢይ አህመድም በኢትዮጵያና ኤርትራ መካከል ያለውንና ለሁለት ዓስርተ ዓመታት የዘለቀውን የNo peace, No war ሁኔታን ከአስመራ ጋር ተነጋግሬ እለውጣለሁ በሚል ተስፋ ለኤርትራ መንግስት ጥሪ ያስተላለፉት በትረ ስልጣኑን የጨበጡበት እለት ባቀረቡት ጥሪ ሲሆን ጥሪያቸውንም ከአስመራ ይልቅ ዋሺንግተን  ቀድማ የወደደችላቸው ይመስል «ሁለቱን

ሀገራት አስታርቃለሁ» ማለታን በጭምጭምታ መስማት ችለናል፡፡ አስመራ ግን ቀደም ብላ ለመለስና ለኋይለማሪያም ባሳወቀችው አቋማ -ማለትም «የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ተግብሩና ባድመን ስትሰጡን ...»በሚለው አቋማ እንደጸናች ለንግግሩ በራን ጠርቅማ ዘግታለች፡፡

በአስመራ በኩል ያለውና ለ16ዓመታት የዘለቀው አቋም ሳይለወጥ የአሜሪካም ሁለቱን የማስታረቅ እቅድና ፍላጎትም ሆነ የአዲሱ ጠ/ም ከአስመራ ጋር እርቅ የማውረድ ዓላማ እንዴት እንደሚያሳኩት ባይታወቅም የመታረቁን አስፈላጊነት ብዙዎች ሲናገሩ ይደመጣል፡፡

የኢትዮጵያ ወደብ አልባማነት ብቻ ሳይሆን በየዓመቱ ለጅቡቲ እምትገፈግፈው መጠን እያደገ መምጣት ይህን ገቢ ለመቀራመት በአሰብ በኩል የመውጪያ መግቢያ በር አመቻችተው የሁለቱን እርቅ የሚጠባበቁና የሚገፋፉ ሶስተኛ ኋይሎችም ሚና ቀላል በማይባል ደረጃ ሁለቱን ለማስታረቅ ሲጥሩ ይስተዋላል፡፡

ሆኖም በሁለቱ ሀገራት መካከል እንደ በርሊን ግንብ የተገነባችው የባድመ ባለቤትነት ጉዳይን በምን መልኩ ሊፈቱ እንደሚችሉ ያሳዩን ቄላቄል አዲስ አቅጣጫ የሌለ ሲሆን ዋሽንግተንም ሆነች ለአስመራና ዱባይ-እንዲሁም ለአዲስ አበባው አዲሱ አመራር የባድመ ጉዳይ የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት በመወሰን ደረጃ ያላትን ኋይል ስልጣንና አቅምን ዛሬም ቢሆን የዘነጉት ይሆናል ማለት ያስቸግራል፡፡ በተለይም የጉዳይ ግንባር ቀደም ተጣቃሚም ሆኑ ተጎጂ የሚሆኑት አስመራና አዲስ አበባ የባድመን ባለስልጣንነትን መሸራረፍ እንኳን የሚቻላቸው አይሆንም፡፡

«ከ30ሺህ በላይ ሀገር ወዳድና ሀገር አፍቃሪ ኢትዮጵያን ውድ ህይወታቸውን መስዋእት ከፍለው ከወራሪው ሻእቢያ ሰራዊት እጅ ነጥቀው በኢትዮጵያ ግዛት ስር አደረጓት » የምትባለዋን የደም መሬቷን ባድመን ማን ለማን ሊሰጠ እንደወሰነ ገና ፍንጭ አላሳዩም፡፡

ዛሬ የባድመ ምድር በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ያለ ብትሆንም ዘ ሄግ እንደለው ዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ውሳኔ ደግሞ ባድመ የኤርትራ ግዛት ተብላ የምትታወቅ አወዛጋቢ የደም ምድር ናት፡፡

ኢትዮጵያ ግዛቴን በሻእቢያ ተወረሬ ተነጥቄያለሁ በሚል ፍትሃዊ አቋምና ውሳኔ እራሷን አደራጅታ በከፈተችው የአጸፋ መልሶ የማጥቃት ወታደራዊ ዘመቻ
አይደለም የተወሰደባትን የባድመን መሬት ማስመለስ መቻል ይቅርና አብዛኛውን የኤርትራን ገዢ መሬት እየተቆጣጠረች ወደ አስመራ እየገሰገሰች ባለችበት ወሳኝ ወቅት ጦርነቱ በኤርትራዊው መለስ ዜናዊ እንዲቆም ከመደርጉም (በተሰነይ በኩል ከ60ኪ ሜ በላይ የሸፈነው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በኮ/ል አታክልቲ በርሄ እየተመራ ወደ አስመራ እየገሰገሰ ባለበት ሰዓት መለስ በአየር ላይ በራዲዮ የጦርነቱ መቆም ያውጃል፡፡ በወቅቱ ከኮ/ል አታክልቲ ሰራዊት ጋር በኤርትራ በረሃ ውስጥ የነበረው የቢ ቢ ሲ ጋዜጠኛ ጠ/ምኒስትር መለስ ጦርነቱ ቆሟል ብሏል አንተስ ምን ትላለህ ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ መኮንኑ እኔ ወታደር ነኝ ታዛዥ-ግን ወደ ድል እየተቃረብን ባለበት ሁኔታ ውጊያውን አቁመህ ቀኝ ኋላ ዙር መባሉ እጅግ አስደንቆኛል በማለት ስራዊቱን ለመመለስ በተገደደበት ወቅት ያንን አጋጣሚ በመጠቀም የሻእቢያ ሰራዊት በወገን ጦር ላይ ከፍተኛ እልቂት እንደፈጸመ ጋዜጠኛው ዘግቧል....ይህንንም ትእዛዝ ያስተላለፈው መለስ ነበር) በላይ ወደ አልጀርስ በመሄድ በአስር ሺህዎች ህይወትና ደም መስዋእትነት የተገኘውን መሬትና ድል አሳልፎ በመስጠት ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ለመሄድ ሊስማማ ቻለ፡፡

ሻእቢያ በጉልበት  ባድመን እንደተቆጣጠረ ሁሉ ኢትዮጵያም መሬቷን እምታስለቅቅበት ኋይልና ጉልበት በማጣት አስታራቂ ተብዬዎች ጉዳዩን ወደ ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት በመውሰድ እዚያ ተዳኙ ብለው ወደ ፍርድ ቤት ብትሄድና ቢፈረድባት ጉዳዩ ዛሬ ካለበት ሁኔታና ደረጃ በተለየ ሁኔታ የሚታይ ሆኖ ሳለ ነገር ግን በኋይል የተያዘባትን መሬት በኋይል ካስመለሰች በኋላ -

1ኛ-ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ለመውሰድ መስማማቱ

2ኛ-የፍርድ ቤቱንም ውሳኔ ይግባኝ በሌለው መልክ እንዲሆን መስማማቱን ስናይ መለስ ለምን ያንን አደረገ ማለት ብቻ ሳይሆን ምን አይነት ሴራ እየፈጸመ ነበር ብለን እንድንጠይቅ በሚያደርጉን ሂደቶች ባድመ የኤርትራ ግዛት ናት ተብሎ እንደተወሰነ ነው ማወቅ የቻልነው፡፡

ሆኖም ይህ በ2002የተላለፈው ውሳኔ ከተላለፈ ከአስራ አምስት ዓመታት በላይ ቢሆንም በኢትዮጵያ በኩል ግን « የፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመርህ ደረጃ ተቀብያለሁ፤ ለአፈጻጸሙ ደግሞ እንነጋገር» በማለት ከአስመራው ሰውዬ ጋር መነጋገሩን በእጅጉ ስትፈልግ በኤርትራ በኩል ደግሞ «ይግባኝ የሌለውን ውሳኔ እቀበላለሁ ከተባለ ድንበር ማካላሉ ይፈጸም፤ባድመም ወደ ግዛቴ ትጠቃለልና ያኔ እንነጋገራለን» በሚለው አቋሙ ከህወሃት መራሹ ስርዓት ጋር ለመነጋገር እንደማይፈቅድ በሚገልጸው አቋሙ እስከዛሬ ጸንቶ እንዳለ ነው ዓለም ሁሉ የሚያውቀው፡፡

የኢትዮጵያና ኤርትራን ግንኙነት ወደ መልካም ጉርብትና ግንኙነት ደረጃ ለማሳደግ ከሁሉ በላይ የባድመን የባለቤትነት መልስ በአጥጋቢ ሁኔታ መመለስ የሚቻለው ሲሆን ብቻ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህን መመለስ የሚቻለው መሪ በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ የመሪነቱን ስፍራ ጨብጧል ተብሎ ከታሰበ የዚህ መንግስት ቀዳሚ ተግባር የሚሆነው አጠቃላይ የፍርድ ቤቱን ሂደትና ስምምነቶቹን ከልሶ በማጥናት አዲስ አይነት የመደራደሪያ እስትራቴጂ ያለው አጀንዳ ይዞ መቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

አንዲት ሀገር የምትፈራረማቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶችን በምታካሄደው የስርዓት ለውጥ ተቀብሎ የማስተናገድና ብሎም ጥቅማን እማያስጠብቁትን ስምምነቶችን ጥላ የመውጣት  መብቷ የተጠበቀ ቢሆንም ወሳኙ ግን ወደ ስልጣን የመጣው አዲሱ አመራር እራሱን በቀድሞ ስምምነቶች የሚያስር መሪ መሆን አለመሆኑ ላይ ነው፡፡

*የባድመን መሬት ወደ ኤርትራ ግዛት ያካለለው የዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዴት ሊተላለፍ ቻለ?

** ፍርድ ቤቱ በሁለቱም ወገኖች የቀረቡለትን ማስረጃዎች፣መከራከሪያዎችና ካርታዎችን እንዴት ነበር የቃኘው?

***በኢትዮጵያ በኩል የተወከሉት ተወካዮችና ያቀረቧቸው የመከራከሪያ ጭብጦች፣ማስረጃዎችና ሙግቶች ምን ይመስሉ ነበር?

***በጾረና በወገን ሰራዊት ላይ በመለስ ትእዛዝ የተፈጸመ ታላቅ ክህደትና የወገን እልቂት ለምን አስፈለገ የሚለውን መልስና

***በባድመ ፍርድ ላይ የመለስ ቀጥተኛ ተሳትፎና ሚና ምን ያህልና ምንስ ይመስል ነበር የሚሉትን ወሳኝ ነጥቦች መልስና ብሎም በጦርነቱ ወቅት በቡሬ ግንባር እየተካሄደ በነበረው ጦርነት ላይ የቢል ክሊንተን አቋምና ለመለስም ያደርግ ዘንድ ነግሮት ያልተፈጸመውን አሰብን የተመለከተ ሁኔታን ያካተተውን ክፍል በቀጣይ አቀርባለሁ፡፡

---------------
**አስተያየትና ጥያቄያችሁን በ**teklu7@gmail.com **ብትልኩ መልስ እሰጣለሁ።**

**ኢትዮሚድያ** - Ethiomedia.com

May 14, 2018